ከታጋይ ሓዱሽ ካሡ

ነሐሴ 25/2004 ዓ.ም

# «የ80 ሚሊዮን ህዝብ እንባ ያበቅላል ዘንባባ»!!

ያልሆነውና ያልተፈጸመውን አልተፈጸመም፡፡ በትክክል ዕውን የሆነውና የተፈጸመውን ደግሞ ተፈጽሟል! ሆኗል! በማለት እቅጩን የመናገር ተፈጥሮ የተላበሰው ኢህአዴግ የሚመራው የኢፌዴሪ መንግስት ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ዕለተ ማክሰኞ ማለዳ፣ ፀሐይ ውሎዋን ለማድመቅ ብርሃን መፈንጠቅ በጀመረችበት ሰዓት ላይ፣ ራሱ መንግስት፣ የኢትዮጵያ ህዝቦችም ሆኑ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ደግሞ-ደጋግሞ ቢሰማው ፈጽሞ ለማመን የተቸገረበት የታላቁ መሪ የታጋይ መለስ ዜናዊ የመሰዋእትነት የመርዶ ዜና አስደመጠ፡፡

ይህንን የመርዶ ዜና የሃገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ የብዙሃን መገናኛ አውታሮችም እየተቀባበሉ በደቂቃዎች በአራቱም የዓለም ማዕዘናት አዳረሱት፡፡ ድፍን አለምም በሐዘን ተውጦ «እሪይ በይ ኢትዮጵያ!! እሪይ በይ አፍሪካ!! እሪይ በይ ዓለም!!» በማለት እምባውን እንደ አባይ ውሃ በጉንጩ እያወረደ ድምጹን ከፍ አድርጎ አሰማው፡፡ አእዋፋትም ያለማቋረጥ የሀዘን ዝማሬ አሰሙ፡፡ ቤተ- እምነቶችም የሐዘን ደወል አቃጨሉ፡፡ከኢትዮጵያ ህዝቦች እየወረደ ያለውን እምባ፣ የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች መሪዎች እንዲሁም የተለያዩ አገራት መሪዎች ያሰሙትን እሪታና ሀዘን የታዘበችው ጀምበርም በክረምቱ ደመናና ጉም ተሸፈነች፡፡ ምድሪቱም የጨለማ ጭጋግ ወረራት፡፡

የኢፌዴሪ መንግስት የኢትዮጵያ ባንዲራ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ብሄራዊ የሐዘን ቀን ማወጁን የሰማው፣ ወንድም የደቡብ ሱዳን ህዝብና መንግስትም ሐዘናችሁ!! ሐዘናችን ነው!! ብለው የሃገሪቱ ባንዲራ ለ 3 ቀናት ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ብሄራዊ የሐዘን ቀን አወጁ፡፡

የ14ኛው ፓራ - ሎምፒክ ተረኛ አዘጋጅ የእንግሊዝዋ ለንደን ከተማም ነሐሴ 24/2004 ዓ.ም ለታጋይ መለስ ዜናዊ የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት በማድረግ ፓራ -ሎምፒኩ እንዲጀመር አድርጋለች፡፡ ከ20 በላይ የሃገራትና የመንግስታት መሪዎችም በታጋይ መለስ ዜናዊ የቀብር ስነ ስርዓት እንደሚገኙ አረጋግጠዋል፡፡

የታጋይ መለስ ዜናዊ - ዜና እረፍት እንደተሰማ የኢትዮጵያ ህዝቦች እንደ ዓይን ብሌናቸው ይመለከቱት የነበሩትን ተወዳጁና ብልሁ መሪያቸው ለዘላለሙ ላይመለስ እርቆ በመሄዱ ለጊዜውም ቢሆን ሰማዩ የተደፋ መሰላቸው፡፡

በአየር ብክለት እየተቃጠለች ያለችው ዓለም ዳግም ህይወት ዘርታ፣ ጥቁር፣ ቢጫ፣ ነጭ፣ ቀይ ቀለም ያላቸው የዓለም ድሃ ህዝቦች፣ የማህበራዊ ፍትህ ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ሽንጡን ገትሮ በዓለም አደባባይ አጥብቆ የተሟገተላቸውን፣ በአበው አባባል «አንድ ለእናቱ» ጠበቃቸው፣ ደከመኝ!! ዓለም በቃኝ!! ብሎ ዘለዓለማዊ እረፍት በመምረጡ ሀዘን በረታባቸው፡፡ ባይተዋርነት እንደተሰማቸውም የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የዘር፣ የቀለም ልዩነት ሳይገድባቸው ከያሉበት ሆነው የሀዘን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በአንድነት አስተጋቡ፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዲሁም ድፍን ዓለም ጥልቅ ሐዘናቸውን ብቻ አይደለም የገለፁት፡፡ ተመራማሪው፣ ፈላስፋውና ሊቀ-ሊቃውንት ታጋይ መለስ ዜናዊ ባለፉት አራት አስርት ዓመታት በነበሩት ፈታኝና እልህ አስጨራሽ መራራ የትግልና የድል ዓመታት ያከናወናቸውና ያስመዘገባቸውን ዘርፈ ብዙ ውጤቶችን አስመልክተው በየፊናቸው ምስክርነታቸውን ለመስጠት ጊዜ አላጠፉም፡፡

የተለያዩ አገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሪዎችና ታዋቂ ሰዎች፣ ታጋይ መለስ “የዓለም ድሃ ህዝቦች ዋልታና መከታ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም አስጠባቂ፣ ሃገሩ ኢትዮጵያን የሚወድ፣ አገሩን ከድህነት አረንቋ እንድትወጣ የጣረና ሚልዮኖች ከድህነት እንዲወጡ ያደረገ ቆራጥና ጀግና መሪ፣ ችግሮች ሲከሰቱ በውይይት የሚፈታ፣ ሰላም ወዳድ፣ ጎረቤት አገሮች አብረው እንዲያድጉ አበክሮ የሰራ፣ ለተለያዩ ችግሮች መፍቻ ቁልፍ ቀማሪ፣ የአዳዲስ ሃሳቦች አፍላቂ፣ ባለራእይ፣ ጮራ ፈንጣቂ፣ የለውጥ ሃዋርያ፣ ትራንስፎርሜሽናል መሪ፣ ዓለም የምትሳሳለት አለእድሜው የተቀጨ መሪ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የአፍሪካና የአለም ድሃ ህዝቦች ውድ ልጃቸውን ተነጠቁ” በማለት በአንደበታቸው ምስክርነታቸውን በይፋ ሰጥተዋል፡፡

በጥቅሉ ከላይ በአጭሩ የተጠቀሙት የመሪዎቹ ምስክርነት፣ የታጋይ መለስ ዜናዊን ማንነትና ስብእና በጥቂቱም ቢሆን ይገልፃሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በመሆኑም መሪዎቹ የሰጡት እውነተኛ ምስክርነት የታጋይ መለስ የታሪክ አካል በመሆኑ፣ በአግባቡ በሰነድ መልክ ተይዞ ለወደፊቱ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ የታሪክ ፀሐፊዎችና ተመራማሪዎች የተባ ብእራቸውን አንስተው የህዝባዊ ገድሉ መሪ የተሟላ ታሪክ ለመፃፍ የሚያስችላቸው የተመቻቸ ዕድል ሊፈጠር ይገባል፡፡

ለአሁኑ ግን የተለያዩ አገራት መሪዎች የታጋይ መለስ ዜናዊን ህያው ተግባር አስመልክተው ከተናገሩት መካከል ለማሳያ ያህል የጥቂቶቹን ለመጠቆም ይሞከራል፡፡ ሆኖም የመሪዎቹን አባባል ወደ አማርኛ ቋንቋ ለመመለስ ቢሞከር አባባሎቹን በትክክል ባለመተርጎም የመልዕክቱን ቁም ነገ ሊያደበዝዝ ይችላል የሚል ስጋት አሳድሯል፡፡ ስለዚህ አንባቢ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ይችል ዘንድ መሪዎቹ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተናገሩትን በአጭሩ እንደሚከተለው ቃል በቃል ማቅረቡ ተመርጧል፡፡

“Today with the death of Prime Minister Meles Zenawi, the poor of the world have lost of their greatest champions,” Ethiopian people that they have lost a committed leader and a champion of children at such a young age” —**GORDON BROWN — FORMER - BRITSH PRIME MINISTER.**

“HUGELY significant figure in Ethiopia’s history, in particular helping guide his country from extreme poverty to an era of economic growth and development” - **TONY - BLAIR FORMER - BRITSH PRIME MINISTER.**

“Inspirational spokesman for African on global issues, and provided leadership and vision on Somalia and Sudan.His personal contribution to Ethiopian’s development, in particular by lifting millions of Ethiopians out of poverty, has set an example for the region.” - **DAVID CAMEROM - BRITSH PRIME MINISTER.**

“As a truth African leader, he achieved much for his country and the entire African continent. The outstanding contributions he made to steering NEPAD and to mediation between the Sudan and South Sudan deserve special recognition.” **Dr Angela Merkel - German Chancellor.**

“I would like to pay tribute, in particular, to his commitment in the service of Africa and of its development as well as his tireless efforts to promote peace and stability in the Horn of Africa.” **Francois HOLLANDE- President of the French Republic.**

“Prime Minister Meles deserves recognition for his lifelong contribution to Ethiopia’s development, particularly his unyielding commitment to Ethiopia’s poor” **BARAK OBAMA — USA President.**

“Meles was an outstanding leader of Ethiopia and a renowned statesman” **Hu Jintao — President of the People’s Republic of China.**

“Meles Zenawi was A towering statesman of Ethiopia and Africa and as a person who effectively articulated and advanced the continent’s interests in international fora. In his death, Ethiopia has lost a remarkable leader whose contribution towards peace, progress and development of his country will be long remembered,” **Manmohan Singh — The prime minister of India.**

“Prime Minister Meles worked hard for the social and economic development of Ethiopia ever since he was appointed as the Prime Minister in 1995. His Excellency played an important role in the region’s peace and stability as a prominent leader of Africa. In the international arena, Prime Minister Meles contributed to the development of Africa by participating in G8, G20, COP17 and other meetings where he often represented Africa as its spokesperson, voicing the African position.” **Mr. Yoshihiko Noda, Prime Minister of Japan.**

“Respected African leader, He demonstrated his strong personal commitment over many years to improving the lives of not just his own but all African people” **JOSE MANUEL BARAROSO EUROPIAN COMMISSION PRESENDENT.**

“Meles would be remembered for his exceptional leadership and advocacy on African issues within and outside the continent as well as for overseeing his country’s Economic growth and development” — **BAN KI-Moon — UN Secretary General.**

“Meles Zenawi has left a legacy of accomplishments on environmental matters, particularly regarding climate change and the green economy.Prime Minister Meles Zenawi contributed to leading Africa’s active engagement in the UN climate change negotiations in his role as Chair of the Meeting of the Committee of African Heads of State and Government on Climate Change. His efforts in mobilizing Africa’s voice on climate change are a clear example of his legacy in advancing Pan-Africanism through intergovernmental processes and dialogue. Mr. Zenawi was a champion of the environment, who believed that Africa needed to embrace a low-carbon, resource-efficient green economy as the central pathway to sustainable development. Under his leadership, Ethiopia developed a comprehensive Climate Resilient and Green Economy (CRGE) Strategy, which has the goal of transforming the country into a carbon-neutral middle income country by 2025.” **United Nations Environment Programme (UNEP).**

“The death of Prime Minister Meles has robbed African of one of its greatest sons — he played an important role in pioneering a new era of hope and growth in Africa, driven as he was by the vision of Ethiopia and Africa’s renaissance” **JEAN PING - Former AU Commission chair person.**

“During his Chairmanship IGAD has shined in the international arena due to his successful management of the volatile situation affecting our Region. He tirelessly worked for peace in Somalia, Sudan, Rwanda, Liberia and Burundi. IGAD’s fraternity will sorely miss this great man with a focused vision and brilliant leadership. His vision of Regional Economic Integration and Infrastructure Development, including the Great Renaissance Dam were inspirational to all. We were greatly honored when His Excellency as the only chairperson to do

so, came to the Secretariat to support and encourage the staff, personally.” **Engineer Mahbub - IGAD Secretary**

“A visionary, dynamic and dedicated leader of Ethiopia and indeed the entire African continent.” His commitment to eradicate poverty in Ethiopia and the transformation of its economy, “manifested in the success of social programs and high growth rates that have lifted millions of people out of poverty. The passing away of prime Minister Meles was “a matter of great sorrow for Africa”,” A dedicated and committed pan Africanist” whose passion for the development and transformation of the continent was obvious in his leadership of African Union process, the new partnership for Africa’s development (NEPAD), the African peer review mechanism (APRM) and the committee of heads of state on climate change, the late prime minister for being exemplary, committed and providing insightful direction to this process, including piloting the African delegation to G20 and G8 meetings.” **MR Abdoulie Janneh** - **under secretary general and executive secretary of the Economic commission for Africa (ECA).**

“Tremendous nationalist leader, who had always let peace come to his neighbors! He was one person who could say in black and white with the position of both countries was respected by both” **BARNABA BENJAMIN SOUTH SUDANESE INFORMATION MINISTER.**

“The passing away of Zenawi is not only a tragic loss to the people of Ethiopia, but to the whole continent, Africa had been robbed of a great pan African and a reliable partner in the struggle to bring about lasting peace and stability as well as the economic emancipation of the continent”**. — Yoweri Museveni— Ugandan President.**

"Brave, wise and prowess African leader who led his people on a path of prosperity" **Omer Al-Bashir, SUDAN President**

“Pragmatic and visionary leader who helped stabilize his country, his death was a “devastating loss” - **MWAI KIBAKI — KENYAN President.**

“In this difficult time, the Government and People of Djibouti express their solidarity to the people of Ethiopia. Meles’ determination to bring his country among the top economic powers in the continent has started yielding fruit. As a role model for courage and conviction, Meles will be remembered for his brave fight against terrorism and violence in the region. Africa has lost one of its best men.” - **Ismael Omar Guelleh**, **President of Djibouti.**

“A significant figure in the Horn of Africa, when it comes to regional security matters, saying they both advocated for lasting peace in the horn of Africa as well as stronger relations between horn of African countries and their people” - **Sharif Sheikh Ahmed, SOMALIA President**

“Ethiopia had lost a dedicated, revolutionary and visionary leader, while Africa has lost a reliable spokesperson, adding that the late Meles would be remembered for the steadfastness in defending the interests of Africa and its peoples.” **Jakaya Kikwete - Tanzania President.**

“Zenawi was a visionary and gallant leader with a genuine concern for the socio-economical transformation of Ethiopia, and Africa as a whole — with a commitment for Africa’s rightful place in the world" **Paul Kagame — Rwandan President.**

“Strong intellectual leader for the continent. In our region, he stood out because of his intellect and his ability to respond to lead dialogue on matter relating to African development. He will be missed in all of our meetings and all of our endeavors”. **ELLEN JOHNSON SIRLEAF - Liberian PRSEDIENT.**

“An exceptional leader who contributed as an active role — player in various continental and global initiatives” — **JACOB ZUMA — South African President.**

“AN outstanding African leader who fought for the transition of the continent” - **THABOO MBEKI - Former South African President.**

“I have seen his performance at the African Union (AU), and it is because of his brilliance that leaders of Africa and I decided to hand over the AU - NEPAD programme to him. His death robs Africa of a Committed, forthright, visionary and fearless leader” **OLUSEGUN ABASANJO — Former Nigerian President.**

“Played a key role in both the region and the African continent” - **Kofi Annan- Former United Nations Secretary- General.**

እዚህ ላይ ከላይ የተጠቀሱት የአፍሪካ፣ የአሜሪካ፣ የአውሮፓ፣ የኤስያና የተለያዩ ዓለም ዓቀፍና አህጉር አቀፍ መሪዎች፣ የታጋይ መለስ ዜናዊን ህያው ተግባር ለመግለፅ የተጠቀመባቸው ወርቃማ አባባሎችና የሰጡዋቸው እውነተኛ ምስክርነቶች ልብ ብሎ ለተገነዘበ ሰው መሪዎቹ ለምን እንዲህ አሉ? የሚል ጥያቄ ቢያስነሳ አያስገርምም፡፡ ምላሹ ግን ቀላል ነው፡፡ ይኸውም በታጋይ መለስ ዜናዊ ሐሳብ አፍላቂነትና ሁለንተናዊ የአመራር ብቃት፣ በኢትዮጵያ ያለውን ተጨባጭ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴና የተመዘገቡ ውጤቶች በትክክል አይቶ ምስክርነት መስጠት ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው ምንም ሳያመነታ ሊናገረው የሚችለው እውነታ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላ አገላለፅ ታጋይ መለስ ዜናዊ የክፍለ - ዘመኑ ክስተት በመሆኑና ህዝባዊ መስመር አንግቦ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ በዋነኛነት ለሀገሩ በአጠቃላይ በአራቱም መአዘናት ላሉት ድሃ ህዝቦች ቤዛ ሆኖ የሚዳሰስ ውጤት በማስመዝገብና በዓለምም ታላቅ መሪ መሆኑ በተግባር በማስመስከሩ ነው፡፡ በአጭሩ ታጋይ መለስ ህዝባዊ ቃለ ምህላውና ተግባሩን አቀናጅቶ ከዓላማው ለአፍታም ቢሆን ፍንክች ሳይል እስከ ህይወቱ ፍፃሜ ድረስ ለህዝብ  በማዋሉ ነው፣ የተለያዩ አገራትና የተቋማት መሪዎች እውነተኛ ምስክርነታቸውን የሰጡት ቢባል ሐቁን መናገር እንጂ ማጋነን አይሆንም፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች በጫንቃቸው ላይ ተንሰራፍቶ ለዘመናት ከኖረው አስከፊ ድህነትና ድቅድቅ ጨለማ ለመውጣት መርፌ ቀዳዳው ጠፍቷቸው፣ ሲገፉት ከነበረው ጎስቋላ ህይወት እንዲወጡ የህዳሴ ችቦ የለኮሰው ታጋይ መለስ መሆኑን፣ የሃገራት መሪዎቹ ስለሚያውቁ ነው እውነተኛ ምስክርነት የሰጡት፡፡

ታጋይ መለስ ድህነት ከስር መሰረቱ ተፈንግሎ እንዲገረሰስም “አንድ አለቃ ነው ያለን እሱም ህዝብ ነው፡፡ አንድ ጠላት ነው ያለን እሱም ድህነት ነው!!” ያለውን ጉዳይም በፅናት ተግባራዊ በማድረጉ ነው፡፡ ታጋይ መለስ በመቶ ዓመታት ሊመዘገብ ቀርቶ ሊታሰብ የማይችል የሚዳሰስና የመጨበጥ ዘርፈ ብዙ ዕድገት ባለፉት 21 ዓመታት እንዲመዘገብ በማድረጉ ነው፡፡ በዋነኛነት በአመራር እጦት፣ በሰው ሰራሽና ተፈጥሮ ችግሮች የተነሳ ከ200 ዓመታት በላይ እርቃናቸውን ቀርተው ያገጠጡ ተራሮችንና ሸለቆዎችንም ታጋይ መለስ በቀረፀው  የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ልምላሜ ተላብሰው የሰው ልጅና እንስሳት የሚቦርቁባት ሁኔታ በመፈጠሩ ነው፡፡

ትላንት የብሄር ብሄረሰቦች እስር ቤት ትባል የነበረችው ኢትዮጵያ፣ “ለእኔ አገር ማለት ህዝብ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ጥልቅ ነው፡፡ 80 ሚልዮን ህዝብ በአንድነት ብናጨበጭብ እንደመጣለን” የሚለውን መርህ

አንግቦ ታጋይ መለስ ዜናዊ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረጉ ነው፣ ከ 75 በላይ የሚሆኑ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች "ልዩነታችን ውበታችን" ብለው በዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ በሰላም፣ በመፈቃቀርና በመቻቻል የሚኖሩባት የሁሉም መነሃሪያ የሆነች ኢትዮጵያ በጠንካራ መሰረት በመገንባት ላይ ያለችው፡፡

በአጭሩ ለረጅም ዓመታት ተበላሽቶ የቆየውን የኢትዮጵያ አሉታዊ ገፅታ በተራ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን፣ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ተጨባጭ ውጤት በማስመዝገብ የኢትዮጵያን አዎንታዊ ገፅታ ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ በመፈጠሩ ነው፣ መሪዎቹ ሳይውሉ ሳያድሩ እውነተኛ ምስክርነታቸውን የሰጡት፡፡

ታጋይ መለስ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያን እንዲሁም የዓለም ድሃ ሀገራት ሕዝቦችን የተመለከተ፣ ዓለም ዓቀፍ መድረኮች በተለያዩ የዓለም ከተሞች በሚዘጋጁበት ወቅት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ከ20 በላይ ሰዓታት አለእረፍት በአውሮፕላን ተጉዞ፣ በሳይንሳዊ ትንተና የዓለም መሪዎችን በማሳመን ድሃ ህዝቦች ድምፃቸው እንዲሰማና ተጨባጭ ውጤት እንዲመዘገብ የላቀ ድርሻ በመጫወቱ እና ይህንን ሐቅ ስለሚያውቁ ጭምር ነው፣ የተለያዩ ሀገራት መሪዎች ታሪካዊው እውነተኛ ምስክርነታቸውን በህልፈተ ህይወቱ ማግስት የሰጡት፡፡

የታጋይ መለስ ማንነትና ህያው ተግባር ኢትዮጵያውያንም በተለያዩ ሃገራዊ ቋንቋዎች ልብ በሚነካና መሳጭ በሆነ አገባብ ገልጸውታል፡፡ ሁሉንም ለመግለጽ ጊዜው ባይበቃም፣ ጀግናው ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ እና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከገለጹት መካከል አንድ ሁለቱን አንስቶ በዚህ ፅሁፍ ጥቂት ማለቱ አይከፋም፡፡

"ኢትዮጵያ ውስጥ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ በእርሻው፣ በአገልግሎት መስጫ፣ በማምረቻ፣ በመሰረተ ልማት፣ በትምህርትና በጤና በአጠቃላይ በሁሉም መስክ በጣም ብዙ ለውጦች አሉ፡፡ የሚዳሰሱ ውጤቶችም ተመዝግበዋል፡፡ "ባለፉት 21 ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ካከናወኗቸው መልካም ተግባራት መካከል ዋናውና ትልቁ ጉዳይ ህዝቡ የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥቶ ወደ ስራ እንዲሰማራ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመቅረፅ ደረጉት ጥረት ነው፡፡ ህዝቡ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ሐዘኑን በመግለፅ ላይ የሚገኘውም፣ በኢትዮጵያ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ስለመጣ እና ሰርተው የሚያሰሩ ባለራዕይ መሪውን በማጣቱ ነው"፡፡

"ለጀግኖች ከሞቱ በኋላ ሐውልት የምንሰራላቸው በህይወት ያለን ሰዎች ይመስለናል፡፡ ሆኖም እንደ ታጋይ መለስ ዜናዊ የመሰሉ ጀግኖች ቋሚ ሃውልቱ የሚሰሩት ራሳቸው በህይወት እያሉ ነው፡፡ለዚህም ነው!! የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በመስዋእትነት ከመለየታቸው በፊት በእያንዳንዱ ዜጋ ልብ የተከሉትን ህያው ተግባራቸው፣ ቋሚ ሀውልት ሆኖ ለዘለአለም እንዲቆም ጥልቅ ሀዘኑን በቁጭት እየገለጸ ያለው"፡፡

"እኛ የጎዳና ተዳዳሪዎች ልብሳችን ቢቆሸሽም የንፁህና ብሩህ አእምሮ ባለቤቶች ነን፡፡ ለዚህም ነው!! ታጋይ መለስ ያመቻቹት እና የፈጠሩትን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመን በኮብል ስቶን እና በመሳሰሉት ስራዎች ተሰማርተን ራሳችንን ለውጠን ለአገራችን የድርሻችንን ሚና በመወጣት ላይ ያለነው፡፡"!! ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ያለን አክብሮትና ፍቅርም ጥልቅ ነው፡፡

ከለጋ እድሜው ጀምሮ ለህዝብ የላቀ ክበሬታ የነበረው፣ በምላሹ እስከ ወዲያኛው ህዝባዊ ፍቅርና ክብር የተጎናፀፈው፣ ታጋይ መለስም በአራተኛው ሀገራዊ ምርጫ ማግስት በመስቀል አደባባይ ለተሰበሰቡት የአዲስ አበባ ኗሪዎችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ንግግር ባደረጉበት ወቅት የመጨረሻ መቋጫው "በታላቅ ትህትና ምስጋናችንን እንገልፃለ!! እጅ እንነሳለ!!" በማለት ጎንበስ ብሎ የገባውን ቃል መሰረት በማድረግ የተቀረጸውን የቀጣይ አምስት ዓመታት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ የተለጠጡ ግቦች ለማሳካት ትላልቅ /ሜጋ ፕሮጀክቶች/ ቀርፆ ወደ ተግባር በመለወጡ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ጨምሮ በአንድ አመት ብቻ ለ1.1 ሚሊዮን ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል፡፡

ከላይ በኢትዮጵያውያን አንደበት የተነገሩት ቁምነገሮች የታጋይ መለስ ዜናዊን መሰረታዊ እምነትና ተግባር የሚያንፀባርቁ እውነታዎች ናቸው፡፡ ይኸውም ታጋይ መለስ ዜናዊ በሀገራችን የተደላደለ ምቹ ስፍራ አግኝቶ ህዝባችንን ለዘመናት ጠፍሮ አላላውስ ያለው በዋነኛነት የአስተሳሰብ ድህነት ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝቦችን እግር ተወርች አስሮ የያዘው የአስተሳሰብ ድህነት እና የድንቁርና ምሽግ መደርመስ አለበት፡፡

"ተኩሰን መግደል ከቻልን ድህነትን ነው መግደል ያለብን" የሚለውን መርህ አንግቦና የኢትዮጵያ ህዝቦችን ከጎኑ አሰልፎ፣ ድህነትን ከነሰንኮፉ ለመቅበር ላለፉት አራት አስርት ዓመታት በዋነኛነት ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ሳይታክት እስከ ህልፈተ ህይወቱ ድረስ ቀንና ሌሊት ሽንጡን ገትሮ የሰራው ታጋይ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ፈጥሮ አዲስ የስራ ባህል ገንብቷል፡፡

ታጋይ መለስ ዜናዊ ሀገር የምትለወጠው በማሽነሪዎች ጋጋታ አይደለም፡፡ ቁልፉ ጉዳይ በምልዓተ ህዝቡ ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥ መጥቶ ህዝቡ ተደራጅቶ የራሱን ፈጠራ አክሎ ሲንቀሳቀስና የተፈጠረውንም ቴክኔዎሎጂ መጠቀም ሲችል ነው በማለት በጽናት የቆመለትን መርህ መሬት ላይ ወርዶ ወደ ነገራዊ ሃይል በመለወጡ ትልቁ ስኬቱ ነው፡፡ ለዚህም ነው!! ሃገርን ሁለት እርምጃ ወደፊት የሚያራምደው የአስተሳሰብ ለውጥ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ በመፈጠሩ በሚልዮን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች በአመት ሁለትና ሶስት ጊዜ ማምረት የቻሉት፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩትም ሚሊየነሮች ለመሆን የበቁት፡፡

ታጋይ መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመኑ ከተሸለማቸው በርካታ ሽልማቶች ሁሉ የላቀው ሽልማቱም፣ በአጭር አገላለፅ በሰብዓዊ ልማት ያስመዘገበው ውጤት፣ በዋነኛነት ደግሞ ምልዐተ ህዝቡ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥቶ ማለትም እያንዳንዱ ዜጋ ማንኛውንም ስራ ሳይንቅ ስራ ክቡር መሆኑን በእምነት ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረጉ ነው፡፡ ወጣቱም በግልና በተናጠል እንደ ትላንቱ ስራን ሳይጠየፍ ያገኘውን መስራት መጀመሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ የልማቱ ባለቤት ህዝቡ ነው የሚለው የታጋይ መለስ መሰረታዊ እምነት በምልዓተ ህዝቡ ዘንድ መግባባት እየተደረሰበት ነው፣ ልማታዊ የአስተሳሰብ ልዕልና የበላይነት የሚያገኝበት ምቹ ሁኔታም ተፈጥሯል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ታላቁ መሪ ታጋይ መለስ ዜናዊ ከህዝቡ እንዲበረከትለት ይመኘው የነበረው ጉዳይም ይህ ነው ቢባል የሚያከራክር አይሆንም፡፡

ለዚህም ነው!! የልማታዊ አስተሳሰብ ባለቤት የሆኑት የኢትዮጵያ ህዝቦች በልማት ሠራዊት መልክ ተደራጅተው ታላቁ መሪ በመስዋእትነት ከተለየበት ማግስት ጀምሮ ምንም ዓይነት ንፋስ ሳያስገቡ፣ **ተከተል አለቃህን! ምታ ነጋሪት! ንፋ እምቢልታ!** በማለት ታጋይ መለስ ዜናዊ እንደአለት ጠንክሮ የጀመሩዋቸውን የኢትዮጵያን ህዳሴ ግቦች ለማሳካት ከምንጊዜውም በላይ ቁርጠኛ መሆናቸውን ቃል እየገቡ ያሉት፡፡

ለዚህም ነው! ታላቁ መሪያችን ታጋይ መለስ ዜናዊ!! አንተ በትጥቅ ትግሉ ወቅትና በሰላማዊ መድረኩ ያጋጠሙህን በቀላሉ የማይታለፉ ስፍር ቁጥር በሌላቸው በጣም ውስብስብ ችግሮች ሳትበገር፣ እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትነህና የኢትዮጵያ ህዝቦችን ከጎንህ አሰልፈህ ባስመዘገብኸው ዘርፈ ብዙ ድሎች ለትውልዶች የሚተላለፍ ዘላለማዊ ደማቅ ህዝባዊ ታሪክ በላብህና በደምህ ፅፈሐል፡፡

የቁርጥ ቀን ልጃችን ጀግናው ታጋይ መለስ! ጋሬጣውና እሾኩን ሁሉ ጠራርገህ ሸክማችንን አቅልለኸዋል!!፡፡ ለአንተም ፈጣሪ አፈሩን ያቅልልህ!! የአሁኑ አዲሱ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚመጡት አራትና አምስት ትውልዶችም በቅብብሎሽ ዳር የሚያደርሱት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂና አቅጣጫዎች በትክክል ቀምረህ ትተህልን በክብር አልፈሃል፡፡ ለአፈፃፀሙ ሐሳብ አይግባህ!!፡፡ ለእኛ ስትል ለከፈልከው መስዋእትነትና ወደር ለሌለው ውለታህም፣ እስከመጨረሻዋ ሴኮንድ የተዋደቅህለት ራእይህን በማሳካት አንተንና ሌሎች ሰማእታትን የመካስ ተራው የእኛ ነው!!፡፡ በየአደባባዩ የገባነውን ቃል ካጠፍን አጥንትህ እሾክ ሆኖ ይውጋን!! አደራህንም አናስበላም ብለን ተነስተናል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነትን እየተዋጋን ድርብ ድል እናስመዘግባለን!! በማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች ቃል ኪዳናቸውን በማደስ ላይ ናቸው፡፡

ውድ ልጃችን! ታጋይ መለስ! የህዳሴው ግድብ ለአንድ ደቂቃ አይቋረጥም ያልኸውን! ቃልህን ሳናጥፍ እየተገበርነው እንገኛለን!!፡፡ የፕሮጀክቱ ሰራተኞች በእልህና በቁጭት 24 ሰዓት ሙሉ እየሰሩ ነው፡፡ ዜጎችና ባለሃብቶችም በእልህ ተነስተው የህዳሴውን ግድብ ቦንድ በመግዛት ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ አንዳንድ መ/ቤቶች በየዕለቱ አንድ ሰዓት በመጨመር በቀን ዘጠኝ ሰዓት ለመስራት እንዲሁም ቅዳሜ ጭምር የስራ ቀን ለማድረግ ወስነዋል፡፡ በአጭሩ የስኳር፣ የብረታ ብረት፣ የባቡር፣ በመንገድ ግንባታ ወዘተ ስራዎችም ተጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ ሁላችንም ጉልበታችን፣ ገንዘባችንን እና ዕውቀታችንን ሳንቆጥብ እና ወዲያ ወዲህ ሳንል ቀበቶአችንን ጠበቅ አድርገን ሦስት ዓመታት የቀሩትን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በወኔ እናሳካለን!!፡፡

“ዞሮ ዞሮ ወደ ቤት፣ ኖሮ ኖሮ ወደ መሬት እንደሚባለው - ሳናስበውና ሳንገምተው በወጣህበት በመቅረትህና ከእጃችን ማምለጥህ ሐዘናችን ጥልቅ ነው፡፡ ያንተ አለመኖር የሚጎድለን ነገር እንዳለም አሳምረን እናውቃለን፡፡ ለዚህም ነው ቢጠራቀም የዓባይን ወንዝ በሶስት እጥፍ የሚበልጥ እምባ ያፈሰስነው፡፡ እምባችንን ያፈሰስነው ግን ተስፋ ስለቆረጥን አይደለም!!፡፡ ይልቁንም 80 ሚሊዮን ህዝቦች በአንድነት ሆነን የትግል አርማህን እና ሰንደቅህን ጨብጠን እንደ አባይ ወንዝ የጎረፈው እምባችን እናበቅልበታለን ዘንባባ ብለን ተነስተናል!!፡፡ አስከሬን በክብር ከሸኘን በኋላ በዋነኛነት ከ2005 ዓ.ም የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ማግስት ጀምሮ አንዲትም ደቂቃ ብትሆን በዋዛ ፈዛዛ ሳናባክን ኢትዮጵያችንን የልማት ዘንባባ እናነጥፍባታለን፡፡”

በአጭር ቋንቋ አንተ የሁሉም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ውድ ልጅ የሆንከው ታጋይ መለስ፣ እድሜ ልክህን የከፈልኸውን መስዋእትነት እና ከኢህአዴግ ታጋዮች ጋር ሆነህ **“የማያልፉት የለም፤ ያ ሁሉ ታለፈ! ታጋይ የህዝብ ልጅ በደሙ በላቡ ደማቅ ታሪክ ፃፈ!!”** ብለህ የዘመርከውን፣ **“በሂወት ዘመን ትግሉና ገድሉ ሁሌም ይወሳል አይሞትም እሱ”** እንዲሁም **“ምነው ሞት ክፉ ተመኘ፣ ተተኪ እንዳለው ባወቀ ሞት እንዲህ ባልተጨነቀ”** እና ሌሎችም መዝሙሮች እየዘመርን ከገነባኸው ጠንካራ ፓርቲና መንግስት ጎን ቆመን፣ በአሁኑ ወቅት በአንድነት ዳግም እንደ አዲስ የተነሳውን የህዳሴው ህዝባዊ ማዕበል በማጠናከር፣ ድህነትን ታሪክ በማድረግ ስምህን በወርቅ ቀለም ጽፈን ለዘለዓለሙ ከመቃብር ላይ በላይ እናኖራለን!!

**“ባለራዕዩ ታጋይ መለስ በመስዋእትነት ቢለየንም ከደማችን ጋር የተዋሃደውን ራዕዩን ህያው እናደርገዋለን!!**

**ቸር ይግጠመን!!**